አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Addis Ababa University

የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት

Office of the Dean of Students

Date: April 30, 2024

No: የ·ተ·ማ/ዲን/429 /16/24

To: **All Colleges/Institutes with Regular Undergraduate Programs**
Addis Ababa University

From: **Dr. Shibru Temesgen**
Dean of Students

Subject: **Student Council/Union Election**

It is to be recalled that we have been establishing student council at college level and student union at University level for the past academic years to have representation of students in all matters that lie within their mandates. The dean of students office has made necessary preparation to conduct the election of student council/ union for the upcoming academic year 2024/2025.

Therefore, this is to urge all deans/institute directors to give utmost priority to establish student council at your own college/institute as per the election protocol attached to this letter and the existing Addis Ababa University student union regulation. This is also to inform you to strictly follow the action plan attached.

With regards

Encl:

- Notices to be posted to all students and college Community (**2 pages**)
- Action Plan for Student Council/Union Election (**1 pages**)

CC

- Office of the President
- Office of the Academic Vice President
- Office of the Vice President for Administration and Student Services
- Director for ICT office
- Director for Student Services
- Director, Standard, Safety and Security
- Student Union Office

Addis Ababa University

☎0111-22-24-20 ✉ 1176 Emai students.dean@aau.edu.et Fax: +251-011-123-9766

ቀን: ሚያዝያ 21, 2016 ዓ.ም

ማስታወቂያ

ለመደበኛ ፕሮግራም የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በሙሉ

ጉዳዩ: የ2017 ዓ.ም የተማሪ ካውንስል/ህብረት ምርጫ ይመለከታል

ሀ)አጠቃላይ መስፈርቶች / CRITERIA FOR STUDENT COUNCILORS/

1. በዩኒቨርስቲው የሚገኙ ኮሌጆች/ኢንስቲቲዮቶች በመደበኛ ፕሮግራም የቅድመ ምረቃ ተማሪ የሆነ/ች
2. ከዚህ በፊት በዩኒቨርሲቲው ምንም አይነት የዲሲፕሊን ቅጣት የሌለበት
3. ከተለያዩ ሱሶች ነጻ የሆነ/ች
4. በ2016 ዓም ተመራቂ ያልሆነ/ች
5. በሚማርበት ኮሌጅ/ዲፓርትመንት ቢያንስ ከ 20 credit hour በላይ (ወይም ተመጣጣኝ ECTS) ኮርሶችን የወሰደ/ች
6. የአጠቃላይ ሴሚስተር ጥቅል ውጤት 2.75 እና ከዛ በላይ ያለው/ላት *(በቀጥታ ለሚወክሉት የአካል ጉዳተኛ ና የሴት ተማርዎች ተወካይን አይመለከትም)*
7. የተማሪ አመራርነት ልዩ ልዩ የሲቪክ አደረጃጀቶች፤ ከክለባትን እንዲሁም በጎ አድራጎት ላይ እንቅስቃሴ ያለው/ላት
8. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በቅንነት፣ በታማኝነት፣ እንዲሁም ከምንም ወገንተኝነት እና ጎጠኝነት አስተሳሰብ ነፃ በሆነ መልኩ ባለው አቅም ጊዜና ችሎታ በበጎ ፈቃደኝነት ተማሪዎች በአግባቡ ማገልገል የሚችል።
9. ያለምንም ክፍያ በነጻ ለማገለገል ፍቃደኛ የሆነ/ች

ለ) የምርጫው ሂደት/SELECTION PROCEDURE/

የምርጫው ሂደት በሚከተለው ቅደም ተከተል ይከናወናል።

1. የትምህርት ክፍል ተወካዩች በዚህ ማስታወቂያ መሰረት ለትምህርት ክፍላቸው ከሚያመለክቱት ተማርዎች መካከል በትምህርተ ክፍሉ አካዳሚክ ኮምቴ ይመረጣሉ:: አመልካች ከለሌ የትምህርተ ክፍሉ አካዳሚክ ኮምቴ አንድ ተማር እንዲወክል ይደረጋል።
2. የትምህርት ክፍል ተወካዩች የኮሌጅ ካውንስል አባላት ይሆናሉ። ለፕሬዝዳንት፣ም/ፕሬዝዳንት እና ፀሐፊ ቦታዎች በበይኔ መረብ/online/ በኮሌጁ ተማርዎች ይመረጣሉ።የአካል ጉዳተኛ ና የሴት ተማርዎች ተወካይን በመጨመር በየኮሌጁ የተመረጡ የተማሪዎች ካውንስል በኮሌጅ ዲን በኩል ለተማርዎች ዲን ያሳውቃሉ።
3. የምርጫ ውጤቱ ሁሉም የኮሌጅ ተማሪዎች እንዲያውቁት በግልፅ ማስታወቂያ ይፋ ይደረጋል ፣ ለማፅከል የምርጫ ቦርድ ውጤቱ ይላካል።
4. በማፅከል የአካል ጉዳተኛ ና የሴት ተማርዎች ተወካይን በመጨመር በየኮሌጁ የተመረጡ የተማሪዎች ካውንስል አባላት በሙሉ ለተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚዎች ምርጫ የሚካሄድበትን ጊዜ፣ቦታና ሰዓት ማሳወቅ::
5. የተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚዎች ይመረጣሉ።የተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚነት የሚውዳድሩት ከ አስራ አንዱ ኮሌጆች የተመረጡት **የተማሪዎች ካውንስል ፕሬዝዳንቶች ብቻ** ናቸው::

<u>ማሳሰቢያ</u> በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የሚያገለግሉ የተማርዎች ካውንስል በሁሉም ኮሌጆች በግንቦት ወር 2016 ዓ.ም ስለሚካሄድ ተማርዎች በሁሉም ደረጃ በንቃት እንዲሳተፉ በጥብቅ እናሳስባለን::

የማመልከቻ ጊዜ: ከሚያዝያ 28, 2016 እስከ ግንቦት 02, 2016 ዓ.ም በስራ ሰዓት

ቦታ: በትምህርት ክፍላቹ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማርዎች ዲን ጽ/ቤት



ቀን: ሚያዝያ 21, 2016 ዓ.ም

ማስታወቂያ


ለመደበኛ ፕሮግራም የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በሙሉ

ጉዳዩ: ለ2017 ዓ.ም የተማሪ ካውንስል ምርጫ የትምህርት ክፍል ተወካዮች መምረጫ ማወዳደሪያ መስፈርት

የትምህርት ክፍል ተወካዮች በዚህ ማስታወቂያ መሰረት ከሚያዝያ 28, 2016 ዓ.ም እስከ ግንቦት 02, 2016 ዓ.ም ለትምህርት ክፍላቸው ከሚያመለክቱት ተማርዎች መካከል በትምህርተ ክፍሉ አካዳሚክ ኮምቴ የሚመረጥ ይሆናሉ::ከታች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አንደኛ የሚወጣው የትምህርት ክፍሉ ተወካይ ይሆናል:: የትምህርት ክፍል ተወካዮች መምረጫ ማወዳደሪያ መስፈርት እንደሚከተለው ይሆናል::

1) አካዳሚያዊ ውጤት (35%): የአጠቃላይ ሴሚስተር ጥቅል ውጤት
2) አጭር ስትራቲጂካዊ ጽሁፍ(20%): በዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያ ቋንቋ (Medium of instruction) ውድድሩን ቢያሸንፉ በተማሪዎች ህብረትና በዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ምን አይነት የአመራር ዘይቤን እንደሚከተሉ የሚያሳይ ከሶስት ገጽ ያልበለጠ
3) የግል ተነሳሽነትና የተግባቦት ክህሎት ማረጋገጫ(10%): ከግቢው ማህበረሰብና ማኔጅመንት አካላት ጋር ያለው ግንኙነት ከዲፓርትመንት ሀላፊ እና ከመምህራን በተማሪው የግል ተነሳሽነትና ተግባቦት ችሎታ ዙሪያ የተሰጡ ማረጋገጫዎች/ ሪኮመንዴሽኖች
4) ማህበረሰብ አገልግሎት(5%): የተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት የተሳተፈ መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል
5) የአመራር ልምድ(15%): ከዚህ በፊት የነበሩ የተማሪ አመራርነት ልዩ ልዩ የሲቪክ አደረጃጀቶች፤ ከክለባትና እንዲሁም በጎ አድራጎት ላይ እንቅስቃሴ ያደረጉበትን ማረጋገጫ (ደብዳቤዎች ወይም የምስክር ወረቀቶች)
6) ልዩ ነጥብ የሚያሰጡ (5%): ፆታ (ሴት 2.5%) ፤ አካል ጉዳተኛ(2.5%) ና ሴትና አካል ጉዳተኛ (5%)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማርዎች ዲን ጽ/ቤት



ቀን: ሚያዝያ 21, 2016 ዓ.ም

ማስታወቂያ

ለ2017 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ካውንስል እና የተማሪዎች ህብረት ለማቋቋም የወጣ የድርጊት መርሐ ግብር

ተ.ቁ	የድርጊት መርሐ ግብር ዝርዝር ተግባር	ጊዜ	ፈፃሚ አካላት
1.	የማዕከል ምርጫ ቦርድ ኮሚቴ መሠየም	ሚያዝያ 22/2016	አካዳሚክ ም/ፕሬዝዳንት የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት
2.	የኮሌጆች ምርጫ ቦርድ እና የምርጫ ታዛቢዎች ኮሚቴ መሠየም	ሚያዝያ 26/2016	የኮሌጅ ዲን
3.	ስራውን ለሚያስተባብሩ አካላት ኦሬንቴሽን መስጠት	ሚያዝያ 30/2016	የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት
4.	በግልጽ በሚለጠፉ ማስታወቂያዎች የተማሪ ካውንስል/አመራር ለመሆን ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ለትምህርት ክፍላቸው እንዲያመለክቱ ማድረግ	ከሚያዝያ 28, 2016 እስከ ግንቦት 02, 2016	የኮሌጅ ዲን
5.	የትምህርት ክፍል ተወካዮችን ከታች በተዘረዘሩት የማወዳደሪያ መስፈርቶች ማስመረጥ እና ለኮሌጅ ዲን ማሳወቅ ሀ) አካዳሚያዊ ውጤት (35%): ለ) አጭር ስትራቲጂካዊ ጽሁፍ(20%) ሐ) የግል ተነሳሽነትና የተግባቦት ክህሎት ማረጋገጫ(10%) መ) ማህበረሰብ አገልግሎት(15%) ሠ) የአመራር ልምድ(15%) ረ) ልዩ ነጥብ የሚያሰጡ (5%)	ግንቦት 5-9/2016	የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ና የትምህርት ክፍሎች አካዳሚክ ኮሚቴ አባላት
6.	የካውንስል ምስረታና የሥራ አስፈፃሚዎች ስም ዝርዝር ለኮሌጅ ማህበረሰብ እና ለሁሉም ኮሌጅ ተማሪዎች አስቀድመው ማሳወቅ	ግንቦት 12/2016	የኮሌጅ ዲን
7.	የኮሌጅ ካውንስል ምርጫ በዩኒቨርስቲው ድረገጽ portal.aau.edu.et በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ የምርጫ ሲስተም (Electronic election system) በመታገዝ ምርጫው በተቀመጠለት ጊዜና ሰዓት እንዲካሄድ ማድረግ።	ግንቦት 16/2016	የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ፤የኮሌጅ ዲን ፤ የኮሌጆች የምርጫ ቦርድ፤ ከ ICT ክፍል ጋር በመሆን
8.	የምርጫ ውጤቱ በሁሉም የኮሌጅ ተማሪዎች እንዲያውቁት በግልፅ ማስታወቂያ ይፋ ይደረጋል እና ለማዕከል የምርጫ ቦርድ ያሳውቃል።	ግንቦት 17/2016	የኮሌጅ ምርጫ ቦርድ እና የኮሌጁ ዲን
9.	የአካል ጉዳተኛ ና የሴት ተማርዎች ተወካይን በመጨመር በየኮሌጁ የተመረጡ የተማሪዎች ካውንስል አባላት በሙሉ የተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚዎችን ማስመረጥ።	ግንቦት 23/2016	የማዕከል የምርጫ ቦርደ
10.	የተመረጡ የተማሪዎች ህብረት ስራ አስፈጻሚዎችን ለማህበረሰቡ ማሳወቅ	ግንቦት 26/2016	የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማርዎች ዲን ጽ/ቤት

የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት
Office of the Dean of Students
Addis Ababa University